# “አርቲክል 19”– የመብት ተሟጋች ወይስ የቀለም አብዮት አዝማች?

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

መቀመጫውን ለንደን ያደረገውና “እኔ ለትርፍ ያልተቋቋምኩ ድርጅት ብሆንም፣ ሃሳብን በነፃነት ለመግለፅ መብትና ለመረጃ ነፃነት ልዕልና ቆሜያለሁ” በሚል ማንነቱን በድረ-ገፁ ላይ ያተተው “አርቲክል 19” የተሰኘው ድርጅት፤ ከመሰንበቻው አዲስ ክስተትን ይዞ ብቅ ብሏል–ድብቅ ማንነቱን በይፋ የሚያሳብቅበትን። እናም ሰሞኑን “ወጡ ሳይወጠወጥ፣ ወስከንቢያው ቁጢጥ” እንዲሉ አበው፤ ገና ከጅምሩ አንጋፋ የሀገራችንን የጋዜጠኞች ማህበራትን በማሳደብ፣ ከፍ ሲልም ተባብሮ የመስራት ራዕይን ከመሰነቅ ይልቅ ስማቸውን በማጠልሸት ምስረታውን የጀመረውና ራሱን “የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ፎረም” በማለት የሚጠራውን ስብስብ ወደ ናይሮቢ “ለስልጠና” በሚል ሽፋን ለቀለም አብዮት ምክክር ጠርቶታል።

ይህ ስብስብ በምስረታው ዕለትና መባቻው ወቅት በተለያዩ ከሙያው ጋር ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦችና ጋዜጠኞች አማካኝነት “ሲፒጄ” ከተሰኘው አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋም ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑ ሲገለፅ እንደነበር አይዘነጋም። እንዲያውም “ማህበሩን” እንዲቋቋም ያደረገውና ከጀርባው ሆኖ የሚያሾረው ይኸው ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይል መሆኑም ጭምር ሲነገር ነበር። እርግጥ ልክ ፀረ-ኢትዮጵያው ተቋም “ሂዮማን ራይትስ ዎች” በሀገራችን ላይ ያሴረው አንድ አሉባልታ ሲታወቅበት፣ እኩይ ምግባሩን እንደ “ኦክላንድ ተቋም” ዓይነት አምሳያዎቹ እንዲያጦዙለት እንደሚያስደርገው ሁሉ፤ “ሲፒጄ”ም ከአዲሱ ስብስብ ጋር የነበረው ሸር ጉድ ሲነቃበት፣ እህት ኩባንያው ለሆነው “አርቲክል 19” እንደ ውርስ ለማስተላለፍ መሞከሩ ብዙም የሚደንቅ አይደለም–እንዲህ ዓይነቱን የፅንፈኞች “የተበላ ዕቁብ”ን ላለፉት ዓመታት ስናየውና ስንታዘበው የመጣነው ጉዳይ ነውና።

ያም ሆነ ይህ ግን በቅድሚያ በ“ሲፒጄ” ስውር አጃቢነት እንዲፈበረክና ኋላ ላይም በ“አርቲክል 19” ለስልጠና (ለ‘ስይጠና’ ቢባል ሳይሻል የሚቀር አይመስለኝም) ወደ ናይሮቢ ያቀናው ስብስብ ገና በምስረታ ላይ ያለና ለሀገር ውስጥ የጋዜጠኞች ማህበር ዕውቅና

በሚሰጠው አካል የማይታወቅ ነው። ታዲያ አንድ ወዳጄ እንዳጫወተኝ ተጠሪ አባላቱ፤ አቶ አያሌው አስረስ፣ አቶ ጌታቸው ወርቁ፣ አቶ ብሩክ ከበደ፣ አቶ ብዙአየሁ ወንድሙ፣ አቶ በትረ ያዕቆብ፣ አቶ ስለሺ ሐጎስ፣ አቶ ነብዮ ሃይሉ፣ አቶ ዘሪሁን ሙሉጌታና አቶ ብስራት ወልደሚካኤል ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች በግል ሚዲያው ውስጥ የሚሰሩና አብዛኛዎቹ ማናቸውም የመንግስት ተግባራት የማይዋጡላቸው ብሎም የሚያዮትን ልማታዊ ስራ እንኳን ሳይቀር በጭፍን ጥላቻ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" እያሉ በመካድ የሚታወቁ እንደሆኑም ጭምር አልሸሸገኝም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ባጎናፀፋቸው መብት መሰረት በሚሰሩት የሚዲያ ተቋማት ውስጥ የሀገራችን ፅንፈኛ ሃይሎች አጀንዳ "አስተላላፊ ቱቦዎች" መሆናቸውን በቅርቡ ለናሙና በተወሰዱ የግል መፅሔቶች ላይ በተደረገው ጥናት መረጋገጡን አክሎ አውግቶኛል።

እርግጥ እነዚህ ወገኖች ህገ-መንግስቱ በሰጣቸው መብት መደራጀታቸውን የሚቃወም የሚኖር አይመስለኝም። ወደ ናይሮቢ በ"አርቲክል19" ለስልጠና ተጠርተው አቅማቸውን የሚገነቡ ከሆነም እሰየው ነው— ሌላው ቢቀር ከጋዜጠኝነት ሙያዊ ስነ-ምግባር አኳያ ስራቸውን ሚዛናዊና ርትዓዊ እንዲሁም እንዳሻቸው እንዲናገሩና እንዲፅፉ ነፃነት የሰጣቸውን ብሎም የመደራጀት መብትን ያጎናፀፋቸውን ህገ-መንግስትና ሀገሪቱ ያፀደቀቻቸውን ህጎች አክብረው ሊሰሩ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባልና። ዳሩ ግን እኔ እስከሚገባኝ ድረስ እንደ "አርቲክል 19" ያሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ይዘውት ከተነሱት ድብቅ ዓላማ አንፃር ሊሰጡ የሚችሉት ስልጠና፤ ጋዜጠኞቹን ለቆየ የቀለም አብዮት አቀጣጣይነት ፍላጎታቸው መጠቀሚያ ሊያደርጓቸው መሆኑ የማይታበይ ሃቅ ነው። ይህም በቀጣዮ ዓመት በሀገራችን ለ5ኛ ጊዜ ከሚካሄደው ምርጫ ጋር የሚያያዝ መሆኑ አያጠያይቅም። እናም አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም ገና ከተመሰረተ ሁለት ወራትን እንኳን ያላስቆጠረና ዕውቅና የሌለውን "ማህበር" ተሽቀዳድሞ 'ካላሰለጠንኩህ ሞቼ እገኛለሁ' ማለቱ ለእኩይ ሴራው ፅንስን ያለ ጊዜው የማዋለድ ያህል የሰነቀውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው። በሌላ አነጋገር ለቀለም አብዩት ሙከራው መደላድል ለመፍጠር ሲል ጊዜው ካልደረሰ እንቁላል ጫጩትን እየተመኘ ነው ማለት ይቻላል።

ታዲያ የዚህን አባባል ዕውነታ ለውድ አንባቢዎቼ አፍታትቼ ማስረዳት እችል ዘንድ የስልጠና ጠሪውን "አርቲክል 19" ማንነት መፈተሽ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ተቋሙን በገንዘብ እየደገፉ እነርሱ የሚፈልጉትን አጀንዳ እንዲያስፈፅምላቸው ላዩ ላይ ሆነው እንደ

ፈረስ 'ቼ!' እያሉ የሚጋልቡበትን ድርጅቶች ማወቅ የግድ ይላል። እናም በአስረጅነት ራሱን የ"አርቲክል 19" የመረጃ መረብን ዋቢ ላድርግ። አዎ! ድረ-ገፁ እንደሚያስረዳው፣ እርሱን የሚደግፉት ድርጅቶች አስር ናቸው። እንዲህም ሲል ስለ ድርጅቶቹ ዕርዳታ ይመሰክራል–"…የእነርሱ ተከታታይ ድጋፍ፣ ቀጣይነት ያለውና ፈጠራ የታከለበት ተፅዕኖ እንድንፈጥር አድርጎናል።…" በማለት። ታዲያ እነዚህን አስር ድርጅቶች መዘርዘር ከቦታ ጥበት አኳያ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በምሳሌነት ሁለቱን ብቻ ማንሳት ስለ ፅንፈኛው ተቋም ማንነት በግልፅ እንድናውቅ ያደርገናል፣ የተሸፋፈነበትን 'ለትርፍ ያልተቋቋምኩ፣ ሃሳብን በነፃነት ለመግለፅ መብትና ለመረጃ ነፃነት የቆምኩ ነኝ' የሚለውን የእብለት ካባውንም ገላልጦ ያሳየናል። እናም ለአክራሪ ተቋሙ ገንዘብ እየሰጡ 'እገሌ በተባለ ሀገር ውስጥ እንዲህ አድርግ' የሚሉትን የግልፅ ማህበረሰብ ተቋምን (Open Society Institute 'OSI') እና የፎርድ ፋውንዴሽንን (The Ford Foundation 'FF') ማንነትንና ተግባራትን በጥቂቱ እንመለከታለን።

'መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሞኒተር' የተሰኘው ድርጅት እንደሚገልፀው፣ የግልፅ ማህበረሰብ ተቋም (OSI) እ.ኤ.አ በ1993 አክራሪ የኒዮ-ሊበራል ሃይሎችን በረብጣ ገንዘቡ በመደገፍ በሚታወቀው ቢሊየነሩ ጆርጅ ሶሮስ አማካኝነት የተቋቋመ ድርጅት ነው። ሶሮስ ድርጅቱን ያቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ፣ እ.ኤ.አ ከ1994 መጀመሪያ ጀምሮ የፖለቲካል-ኦኮኖሚ አስተሳሰባቸውን ለማከናወን ፈቃደኛ የሆኑ ተቋማትን "በግልፅ ማህበረሰብ ተቋም" ስር በማቀፍ እርሳቸው የሚከተሉትን የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም 'ጣጣን' በሌሎች ላይ በሃይል እንዲጫኑ ማድረግ ነው። ታዲያ እዚህ ላይ 'ለመሆኑ ጆርጅ ሶሮስ ማን ናቸው?' የሚል ጥያቄ ማንሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል–የተቋማቱን ህቡዕ ስብዕና ለመገንዘብ ፈጣሪያቸውንና አስተማሪያቸውን ማወቁ አይከፋምና።

አዎ! እርግጥ ጆርጅ ሶሮስና "አርቲክል 19"ም ሆነ እንደ "ሂዩማን ራይትስ ዎች" ያሉ ፅንፈኛ ተቋማት አባትና ልጅ ናቸው፡፡ ሚስተር ሶሮስ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሊስት ናቸው፡፡ ፖለቲካል- ኢኮኖሚያቸውን ተምረው፣ አስተምረዋል– በገንዘባቸው፡፡ ታዲያ እኚህ ቢጠሯቸው የማይሰሙት ቱጃር፣ እርሳቸውን መሰል አንድ በመቶ (1%) ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረገው ኒዮ-ሊበራሊዝም እያደር እየፈካና እንደ አሮጌ ወይን እየጣመ እንዲኖርላቸው የሚመኙ አሮጌ አክራሪ ነው፡፡ የሚመኙ ብቻም ሳይሆኑ፣ የርዕዮት ዓለሙን ህልውና ለማስጠበቅ በገንዘባቸው ታግለው አታግለዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ2010 የወጣ አንድ መረጃ

እንደሚያመለክተው፤ ሰውዬው ለ"ሂዮማን ራይትስ ዎች" ብቻ የመቶ ሚሊዮን ዶላር የስራ ማስኬጃ አበል ከፍለዋል–'ሃሳብህ ሃሳቤ፣ ዘፈንህ ዘፈኔ' በማለት ኒዮ-ሊበራሊዝምን እንዲሰብኩላቸውና እንዲያስፋፉላቸው፡፡

ዳሩ ግን ሁላችንም እንደምንገነዘበው፤ የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል- ኢኮኖሚ ስርዓት መንግስት ህግና ስርዓትን ከማስከበር ውጭ በኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ፍጹም ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክል ሶሮሳዊ ሰበካ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር ለባለ ሐብቱና ለገበያው የሚሰጥ መረን የለቀቀ ፍልስፍና ነው— ሚሊዮን ድሆችንና ጥቂት ቱጃሮችን የሚፈጥር የእፍኝ ልሂቃን ፍልስፍና። እናም ስርዓቱ መንግስት ቀጭጮና ዳር ቆሞ ጥርሱን ከመንከስ በስተቀር ምንም እንዳያደርግ ያስገድዳል። ፍልስፍናው ብዙዎችን ውጧል፡፡ ሚሊዮኖችን በማዕበሉ አስጥሞ ጥቂቶችን ባለፀጋ አድርጓል፡፡ ግና ዛሬ በዘመናችን ርዕዮተ- ዓለሙ የማይፈለግ ብቻ ሳይሆን የሚያበላላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እናም አፍሪካዊያን ኒዮ -ሊበራሊዝምን በመቃወም የራሳቸውንና ከታሪካቸው፣ ከባህላቸውና ከነባራዊ ሁኔታቸው ጋር የሚጣጣም የፖለቲካል-ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመዘርጋት ተገደዋል፡፡ ውጤታማም ሆነዋል፡፡

ታዲያ "አርቲክል 19"ንና ግብረ አበሮቹን ሁሉ የሚያስቆጣቸውና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚያሯሩጣቸው፣ ከፍ ሲልም ታዳጊ ሀገራትን በቀለም አብዮት ለመናጥ አንዴ የሀገር ውስጥ ክንፍ የሚሆኑላቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማደራጀት ሌላ ጊዜ ደግሞ የሀገር ፍቅር የሌላቸውን ኪራይ ሰብሳቢ ጋዜጠኞችን በስልጠና ሰበብ የሚያሰየጥኑት ብሎም የቀለም አብዮትን ዝናር የሚያስነግቱበት፣ ይኸው አሮጌ አስተሳሰብ ቀስ በቀስ ከገበያው መውጣትና የአፍሪካዊያን አዲሱ አስተሳሰብ ፍሬማ መሆን ነው፡፡ እርግጥ ዘመናዊው ርዕዮተ ዓለም እንደ ጆርጅ ሶሮስ ያሉ የባህር ማዶ ከበርቴዎች መዝባሪነትን ይነፍጋል፡፡ የታዳጊ ሀገራትን ህዝቦች ርካሽ ጉልብትና ድንግል መሬት እንዲሁም የተትረፈረፈ ማዕድን ለመዛቅ ምቹ መደላድሎችንም አይፈጥርም፡፡ እናም ኒዮ- ሊበራሊስቶች አይወዱትም፡፡

በሶሮስ ዳረጎት ሰጪነት የሚንቀሳቀሰው "አርቲክል 19"ኝም እንደ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራሊዝም አገልጋይነቱ አይወደውም–የታዳጊ ሀገራትን አካሄድ፡፡ ያም በመሆኑ ማምሻም ዕድሜ ነውና የሚያመጣው ለውጥ ባይኖርም፤ የርዕዮተ ዓለሙን ህልውና ቢያንስ ለማዘግየት ይንፈራገጣል፡፡ መንፈራገጡ ግን በቀጥታ አይደለም፡፡ በተዘዋዋሪ ነው፡፡ በዘመናዊ እጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ ዘዴ፡፡ በዚህም ርዕዮተ ዓለሙን የሚያቀነቅኑ ነገር ግን በስም መልካምነትን የታጠቁ ዘማቾችን በታዳጊ ሀገራት ላይ አሰማርቷል፡፡ በገዳዳ አሮጌ

ፍልስፍናቸው ተልፈስፍሰው ብዙ ታዳጊ ሀገራት በመንገድ ላይ መቅረታቸውም አይዘነጋም፡፡ እንግዲህ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ተሚጋች ነኝ ባዩ ተቋም፣ ከኒዮ - ሊበራሊስቶች ተላላኪ አንዱ መሆኑ ነው–"ኮሚሽን" እየተከፈለው የሚሰራ የቀለም አብዮት አዝማች። ታዲያ ድርጅቱ ስለ ሰው ልጆች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት መከበር እንደሚሰራ በድረ-ገፁ ላይ ቢያትትም፣ ምግባሩ ግን የሶሮስ መሆኑን ማንም ይገነዘበዋል፡፡ ምክንያቱም በሰንሰለታዊ ቁርኝት አማካኝነት ከጆርጅ ሶሮስ ወደ "ግልፅ ማህበረሰብ ተቋም" (OSI) ከዚያም ወደ "አርቲክል 19" በሚደርስ ዶላር አማካኝነት የሚንቀሳቀስ ስለሆነ ነው። ይህም ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውና በምስረታ ላይ የሚገኝ "ማህበር"ን አባል የሆኑ ጋዜጠኞችን ለእኩይ ምግባሩ የጠራቸው ጆርጅ ሶሮስ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው–አክራሪው ተቋም የተወጣው በሽፋን የሚያከናውነውን የተላላኪነት ተግባሩን ብቻ ነውና።

ሌላኛው "የአርቲክል 19" ዳረጎት ሰጪ "ፎርድ ፋውንዴሽን" (FF) የተሰኘ ድርጅት ነው። የድርጅቱ የአክራሪነት ድርሳነ-ታሪክ እንደሚያመለክተው፣ በዓለም ላይ የሚገኙ በሺህዎች የሚቆጠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (NGOs) የሚረዳ ተቋም ነው። ፋውንዴሽኑ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2001 ዓ.ም በደርባን ባካሄደው ኮንፍረንስ ወቅት፣ ፅንፈኛ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (መያዶችን) በገፍ ከረዱት አክራሪዎች መካከል ዋነኛው እንደነበር አይዘነጋም። እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ መባቻ ወቅት ሶስት ቢሊዮን እንዲሁም በ2000 ዓ.ም 13 ቢለዮን ዶላር አጠቃላይ ሃብት የነበረውና ዓመታዊ በጀቱም አምስት ሚለዮን ዶላር እንደሚጠጋ የሚነገርለት ይህ ተቋም፣ በአሜሪካ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ነው–በተለይም በሀገሪቱ የስለላ ድርጅት ሲአይኤ (CIA)።

ጀምስ ፔትራስ የተባሉ ፀሐፊ 'ፎርድ ፋውንዴሽንና ሲአይኤ' (The Ford Foundation and the CIA) በሚል ፅሑፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት፣ በፋውንዴሽኑ እና በስለላ ድርጅቱ መካከል ያለው ግንኙነት የዋሽንግተን አስተዳደርን አሃዳዊ የዓለም ገዥነት ለማጠናከር እንዲሁም ግራ-ዘመም ፖለቲካዊና ባህላዊ ተፅዕኖዎችን ለመድፈቅ በሽፋንነት ፋውንዴሽኑን ለመጠቀም ሆን ተብሎ የታቀደና የጋራ ጥረትን በማካሄድ ላይ ያለመ ነው። በዚህ ተግባሩም የጥቂት አክራሪዎችን ጥቅም በማስጠበቅ የሚታወቀው ይህ ተቋም፣ በየሀገሩ የመንግስት ተቃዋሚዎችን በመርዳት ይታወቃል። ጆአን ሬሎፍስ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ባሳተሙት "The Mask of Pluralism" በተሰኘ መፅሐፋቸው ላይ ይህን ዕውነታ እንዲህ ሲሉ ያረጋግጡታል–"በተለያዩ መንግስታት ምልከታ ፅንፈኞች ተብለው የተገለሉ ግለሰቦች

በፋውንዴሽኑ 'እንኳን በደህና መጣችሁ' ከመባል ባለፈ ዕውቅና ይሰጣቸዋል። የአመፅ ተግባራትን ሽፋን የሚሰጡ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትም በተለያዩ ሀገሮች እንዲከናወኑ ይደረጋል።…"

እንግዲህ ከዚህ ሃቅ በመነሳት አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ የምንችል ይመስለኛል። ይኸውም ፋውንዴሽኑ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ያካሄድ የነበረውን የአሜሪካ መንግስትን "ኮሚኒዝም ወይም ዴሞክራሲ" ህልዮት በግዳጅ የማስመረጥ የበላይነት አሰራሩን፣ ዛሬ ላይ "ሽብርተኝነት ወይም ዴሞክራሲ" በሚል ቀኖና ቀይሮት ከአሜሪካ ፖሊሲ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ሀገራት ውስጥ ጣልቃ እየገባ የሚሰራ መሆኑን ነው። ለዚህም ነው– ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ጀምስ ፔትራስ የተባሉት ፀሐፊ "ፋውንዴሽኑ ፀረ-ኒዮ-ሊበራሊዝም አቋም ያላቸውን ጋዜጠኞችንና አሰራሩ ዴሞክራሲያዊ አለመሆኑን የሚተቹ ሃይሎችን ለመድፈቅ ሲል፣ በተለያዩ ስያሜ የተቋቋሙ ድርጅቶችንና ምሁራንን በመቅጠርና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ በሽፋንነት 'አዲሱን ባህላዊ ቀዝቃዛ ጦርነት' በመምራት ላይ ይገኛል" ሲሉ የተቹት።…ያም ሆነ ይህ ግን ይህ ሃቅ በ"አርቲክል 19" መልማይነት ናይሮቢ ለ"ስልጠና" የተጠሩት የሀገራችን የግል ጋዜጠኞች ታጥቀው የሚመጡት የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን አለመሆኑን በገሃድ የሚናገር ነው– የሚቀስሙት ነገር ሃላፊነት ከተሞላበት ሙያዊ አሰራራቸው ይልቅ፣ እንደ ዝናር የሚታጠቁት የቀለም አብዮት አቀጣጣይነትን ነውና።

እርግጥ ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው ሁለት የ"አርቲክል 19" ዳረጎት ሰፋሪዎች ማንነት የምንረዳው ነገር ቢኖር፣ ተቋሙ ከተቋቋመበትና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር አንቀፅ 19 ላይ ከወሰደው ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ስያሜው ጋር ምንም ዓይነት ቁርኝት የሌለው መሆኑን ነው። "ሰይጣን ላመሉ ከመፅሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል" እንደሚባለው ስያሜውን ወስዶ ራሱ ላይ ለማደናገሪያነት ለጠፈው እንጂ፣ ቡድኑ በታዛነት ከተጠለለበት ጉዳይ ጋር ሆድና ጀርባ ነው–"አልተገናኝቶም" እንዲል የሀገሬ አርሶ አደር። እናም 'ማንነቱን በጭንብል ጀቡኖ ድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳን የሚያራምድ ፅንፈኛ ድርጅት' የሚለው እሱነቱ ይበልጥ ስለሚስማማው፣ እዛው ናይሮቢ ውስጥ በሚያደርገው የቀለም አብዮት ዱለታው ላይ በምክረ-ሃሳብነት (Proposal) አቅርቦ ቢያፀድቀው ምናልባትም አመኔታን የሚያስገኝለት ይመስለኛል፡፡ (ውይ የእኔ ነገር!…ዋነኛ ወሳኙንና የቀለም

አብዮት ፈታውራሪውን አባባ ሶሮስን ዘንግቻቸው ተላላኪውን ወስን አልኩት እንዴ?!...ቂ.ቂ.ቂ.....)

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል–"አርቲክል 19"ኝም ሆነ አምሳያዎቹ በሀገራችን ፖለቲካዊ ሂደት ውስጥ ጣልቃ በመግባት እንዳሻቸው መፈትፈት ይችላሉን?" የሚል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በየትኛውም ሀገር ውሰጥ አንድ የውጭ ዜጋ ወይም ድርጅት "ተግባሩን ለማከናወን" ሲል ዜጎችን ተክቶ ስለ ፖለቲካዊ መብታቸው መከራከር አይችልም፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም ሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ መብቶች ለሀገሪቱ ዜጎች ብቻ የተሰጡ በመሆናቸው ነው። ከዚህ አኳያ "አርቲክል 19" የውጭ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (መያድ) እንደመሆኑ መጠን፣ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል አጀንዳውን ለማራገፍና ገና ለገና 'የኢትዮጵያ ምርጫ 2007 ስለተቃረበ የቀለም አብዮት ለማካሄድ ምቹ ሁኔታን እፈጥራለሁ' ብሎ እንዲሁም 'ለሁከት አቀጣጣይነት ይመቹኛል' ያለውን ዕውቅና የሌለው "ማህበር" አባላትን በመሰብሰብ ያካሄደው ግልፅ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት በምንም መልኩ ተቀባይነት የለውም። ቀደም ሲል የገለፅኳቸውን የግል ጋዜጠኞች 'ላሰልጥናችሁ' ብሎ ወስዶ የቀለም አብዮት አዝማች በመሆን እያከናወነ ያለው ተግባር፣ የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት የመዳፈር ድርጊት መሆኑንም ሊያውቀው ይገባል።

እርግጥ የዚህ ፅሑፍ አንባቢዎች ተቋሙ መሰል ተግባራትን መከወን የጀመረው ዛሬ አለመሆኑን እንደምትረዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አዎ! አክራሪው ድርጅት በተለያዩ ወቅቶች ሲፒጄን ከመሳሰሉ የቀለም አብዮት አጋሮቹ ጋር በመሆን 'በል!' ተብሎ የታዘዘውን እንቶ ፈንቶ ወሬዎችን እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋባ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ሲፈተፍት ነበር– እንደ ግብረ-አበሮቹ ጥረቱ መና ሆኖ ቢቀርም።... "አርቲክል 19" የጋዜጠኞችን አንድ ጉዳይ ሲሰማ የተለመደ ጭንብሉን ተከናንቦና ደረቱን እየመታ የአዞ እምባውን ከማንባት የማይመለስ ሃፍረተ-ቢስ ቡድን ነው። ሌላው ቀርቶ በያዝነው የፈረንጆች ዓመት መጀመሪያ ላይ ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ 'ኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት አልተከበረም' በማለት በሀገራችን የፍትህ ስርዓት ጣልቃ በመግባት፣ በከወኑት የወንጀል ድርጊት በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ግለሰቦች ቤተሰቦችን በማነጋገር ዘጋቢ ፊልም እስከ መስራት የደረሰ የአስገራሚዎች ስብስብ ነው። እዚህ ላይ ራሱ ጠይቆ ራሱ ስለሚመልሰው ዘጋቢ ፊልም ተብዬው ምንም ማለት ባልፈልግም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎች ሃሳባቸውን መግለፅ የማይችሉ ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ ፅንፈኛ ተቋሙ

ለቀለም አብዮት እኩይ ምግባሩ ስልጠና የጠራቸው ግለሰቦች ከቶ ከየት ይገኙ ነበር?...ቡድኑ በሀገራችን ያለውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ሳያውቀው ቀርቶ ነው እነዚያን የግል ጋዜጠኞች በተለመደው የህዝብን አመለካከት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መንገዶች እንዲያዛቡና ለሁከት እንዲያነሳሱ በስልጠና በማጥመቅ ሊያዘምታቸው ያሰበው?...አይ "መጥምቁ-አርቲክል 19"!?...መቼም እንዲች...እንዲች ያለችውን ጨዋታ "ስንተዋወቅ አንተዋወቅ" ብለን ብናልፋት ማፌያ ይመስለኛል– ሃቁ ያገጠጠና ያፈጠጠ ነውና።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ህገ-መንግስታዊ እውቅና እና ከለላ የተሰጠው ብሎም በመተግበር ላይ የሚገኝ እንጂ፣ አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም እንደሚያስወራው ይህን ያህል የገዘፈ ችግር ያለበት ጉዳይ አይደለም። እርግጥ የስራው ፈፃሚዎች ሰዎች እንጂ መልዓክት ባለመሆናቸው ጥቃቅን ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ሁሉም ነገር "ምሉዕ በኩሉኼ" ነው ሊባል አይችልም። ለነገሩ እንኳንስ የዴሞክራሲ መብቶችን መከተል ከጀመረች ሁለት አስርታትን ትንሽ እልፍ ያለች ጀማሪ ሀገር ቀርቶ፣ የዳበረ ልምድ ያላቸውና ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ በመስኩ የተጓዙት ምዕራባውያንም ቢሆኑ በርካታ ህፀፆች አሉባቸው።

ኧረ ለመሆኑ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ እነ "አርቲክል 19" 'የንጉሳውያን ቤተሰቦችን ተችቷል' በማለት የእንግሊዝ መንግስት ፕሬስ ቴሌቪዥንን ሲያግደው የት ነበሩ?...በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ ወቅት ኒዮ-ሊበራሊዝምን በማውገዝ ከ1400 ከተሞች በላይ አደባባይ የወጡት የአሜሪካ ዜጎች 'የዜና ሽፋን እጅግ አናሳ ነበር' ሲባልስ ፅንፈኞቹ የሃሳብ ነፃነት ካባ ደራቢዎች የማንን ጎፈሬ ያበጥሩ ነበር?...ዕውን ለፅንፈኞቹ እነዚህ ጉዳዮች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን የሚደፈጥጡ አይደሉምን? ወይስ እነዚህ ጉዳዮች መከሰታቸውን የሚነግሩን "ዳቦአቸው" ሲቋረጥ ነው?...ለነገሩ የእነ "አርቲክል 19"ን ማንነት 'ዊኪሊክስ' የተሰኘው ምስጢር በርባሪ ድረ-ገፅ በይፋ ገልፆታል።...

ነገሩ እንዲህ ነበር።...ጊዜው የዛሬ ሶስት ዓመትን ትንሽ እልፍ ቢል ነው። ወቅቱ ዊሊያም አሳንጄና ባልደረቦቻቸው የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትን ምስጢራዊ መረጃ ይፋ ያደረጉበት ነበር። ኢትዮጵያን በተመለከተም ድረ-ገፁ "አርጋው አሽኔ የተባለ ጋዜጠኛ መረጃዎችን አዲስ አበባ ለሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ያቀብላል" የሚል ዘገባ ያቀርባል። አርጋው አሽኔ የተባለው ሰውዬም ነገሩ "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" ሆኖበት ነው መሰል

ጉዳዩን ለቪዛ ማስመቻነት ተጠቅሞ በራሱ ጊዜ ከሀገር እብስ ይላል። ታዲያ ሲፒጄ የተሰኘው "የአርቲክል 19" እህት ኩባንያ ከርዕዮተ -ዓለም ልዩነቱ ተነስቶ እንደለመደው የኢትዮጵያን መንግስት የማይመለከተውን የአርጋው አሼኔን የመጥፋት ጉዳይን በማጎንና በማብጠልጠል "ዊክሊክስ የሚያወጣቸው ምስጢሮች በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉ ጋዜጠኞችን አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያዊው አርጋው አሼኔ የተባለ ጋዜጠኛ ከሀገሩ እንዲሰደድ አድርጓል፡፡ ይህም የአደጋው አንዱ አመላካች ነው፡፡ …" የሚል ዲስኩር ያሰማል፡፡

ዳሩ ግን እንኳንስ የእነ ሲፒጄን ማንነት ቀርቶ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትንም ምስጢር ሳይቀር ፈልፍሎ በማውጣት የሚታወቀው ዊክሊክስ "…ሲፒጄ ስራው ለጋዜጠኞች መብት መቆርቆር አለመሆኑን እናውቃለን፡፡…" ሲል አጭር ምላሽ ሰጥቶታል፡፡ ይህም በጋዜጠኞች መብት ስም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ቁማርተኞች ስያሜያቸውና ድርጊታቸው የማይተዋወቁ መሆናቸውን መረጃ መረቡ ለዓለም ህዝብ ያረጋገጠበት ወሳኝ ምስጢር ነው ማለት ይቻላል፡፡ እስቲ ለማንኛውም "ውስጡን ለቄስ" ብለን እንለፈው።

ያም ሆነ ይህ ግን ሀገራችን ውስጥ ስር በመስደድ ላይ የሚገኝ ሃሳብን የመግለፅ መብት የተረጋገጠና ገቢራዊ እየተደረገ መሆኑን ፅንፈኛው ቡድንም ቢሆን "ለዳቦው" ብሎ ሊለፍፍ ካልፈለገ በስተቀር የሚያጣው አይመስለኝም። ሌላው ቀርቶ አክራሪው ድርጅት የግል ጋዜጠኞቹን ናይሮቢ ድረስ የጠራቸው ይህን መብት በተሟላ ሁኔታ ሊያስተናግድ የሚችል ምህዳር መኖሩን ስለሚያውቅ ነው። ግና ይህ መብት በሀገራችን እየተፈፀመ ያለው ማንንም ለማስደሰት አለመሆኑን ቡድኑ ማወቅ ያለበት ይመስለኛል–መንግስት ልክ እንደ ሌላው ዴሞክራሲያዊ ተግባራቱ ሁሉ፣ የዜጎች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታችን የሚያበረክተውን የላቀ አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ። እናም የአክራሪው ኒዮ-ሊበራል ድርጅት አሉባልታ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንዲሉት ዓይነት ከመሆን የሚዘል አይደለም።

በመሆኑም ፅንፈኛው ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ ኃይሎች ተፈትፍቶ የሚቦካ የፖለቲካ ምህዳር የሌለ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል። ኢትዮጵያዊያን በታሪካቸው ባንዳዎች ያጋጠሟቸው ቢሆንም፤ ለእንዲህ ዓይነቱ የባዕዳን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ተንበርካኪዎች ሆነው አያውቁም፡፡ ዛሬም የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በታሪካቸው በፈለጉት የፖለቲካ ህልዮት መስመር የመመራት ሉዓላዊ የስልጣን

ባለቤትነታቸውን እንኳንስ በአሉባልታ ቀርቶ በሌላም መንገድ ቢሆን ለማንም አሳልፈው የማይሰጡ መሆናቸውንም ጭምር መረዳት አለበት። ጃጅቶ ከዘራ የያዘ ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ርዕዩተ-ዓለም ጣጣን ለመቀበል የቀለም አብዮትን ማስተናገድ አይፈልጉም–ራሳቸው ወደውና ፈቅደው ባፀደቁት ህገ-መንግስት ላይ ያሰፈሯቸውን ፖለቲካዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን እያጣጣሟቸው ነውና። እናም ቡድኑ እያንኳኳ ያለው የተሳሳተ በርን በመሆኑ፤ ምናልባትም የሚሰማው ካገኘ ይህን የህልም እንጀራውን በተጠማቂዎቹ ግለሰቦች አሸክሞ ወደ ሌላ አካባቢ ማንዣበብ እንዳለበት ሳልመክረው ማለፍ አልሻም። ለምን? ካለ፣ ልክ ሰሞኑን ወደ ሩሲያ በተቀላቀለችው ክሪሚያ ግዛት ውስጥ አስተዳዳሪዎቿ ለሰላማቸው ሲሉ የእነ “አርቲክል 19”ን ጉዳይ ፈፃሚዎች ድርጊት በመግታታቸው ሳቢያ ፅንፈኛው ቡድን “የታሰሩት አክቲቪስቶቼ እንዲፈቱ እይቃለሁ” በማለት ኪሳራውን በመግለጫ እንባው እንዳወራረደው ሁሉ፤ እዚህ ሀገር ውስጥም በቀለም አብዮት ስሌት ዜጎችን በጎዳና ላይ ነውጥ እርስ በእርስ የማስተላለቅ ዓላማን፣ አዝማችንና ዘማችን የሚሸከም ህዝብም ሆነ ምህዳር ስለሌለ ነው። ቸር እንሰንብት።